# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

### የክረምት ስድስተኛ እሑድ ሰንበት

የቃሉ ትርጉሜ ስርወ ቃሉ ከርመ፣ ከረመ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጐድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። የክረምት ዘመን ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ያዐርግ ደመናተ እምአጽናፈ ምድር
ወገብረ መብረቅ ለጊዜ ዝናም
ዘያወጽኦሙ ለነፋሳት እመዛግብቲሆሙ

ከምድር ዳር ደመናት ያወጣል
በዝናብ ጊዜ መብረቅን አደረገ
ነፋሳትንም ከመዛግብቱ ያወጣል

መዝ ፩፻፴፬፥፯

ወንጌል፥ ፮፥፵፯-ፍጻሜ
ቅዳሴ፥ የኤጲፋንዮስ (ዐቢይ)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

«በሰንበት ቦአ ኢየሱስ ምኵራቦሙ ለአይሁድ»
«ኢየሱስ በሰንበት ወደ አይሁድ ምኵራብ ገባ»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ቲቶ ፫፥፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፬፥፯-፲፪ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፯፥፩-፲፯ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# በባሕር ላይ ተራመደ

ከበረከተ ሕብስት በኋላ ማለትም አምስቱን እንጀራ እና ሁለቱን ዓሣ አምስት ሺህ ወንዶች (ከሕጻናት ከሌሎች ሌላ) ተመግበውት አሥራ ሁለት መሶብ እንጀራ ከተረፈ በኋላ ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ወደ ቤተ ሳይዳ ቀድመውት እንዲሻገሩ አዘዛቸው። ከዚያም ትቶአቸው ሲጸልይ ወደ ተራራ ወጣ። በመሸ ጊዜ ጀልባ በባሕር መካከል ነበረች፤ ጌታም በየብስ ነበረ፤ ተራራም በርትቶባቸው ስለነበር ደቀመዛሙርቱ ከመቅዘፊያቸው ጋር ሲታገሉ አያቸው። በአራተኛው ክፍለ ሌሊት ገዳም በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ። በአጠገባቸውም አልፎ ሊሄድ ነበር። ነገር ግን በባሕር ላይ እየሄደ ባዩት ጊዜ ከመምህራችን ጋር በገሊላ ያሳደደነው በጌርጌሶንም ያስጨነቅነው ጋኔን መምህራችን በሌለበት ሊያጠቃን መጥቶ ነው ብለው ባዕድ መንፈስ መስሏቸው ደንግጠው ነበርና ጌታ ግን አይዟችሁ! እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው፤ እርሱም ሐዋርያት በተሳፈሩበት ባሕር ሞገድ ያንገላታት በነበረችው ጀልባ ላይ ወጥቶ አብሯቸው ሆነ፤ ነፋሳቱም ተወ፤ እነርሱም እጅግ ተደነቁ (ማር ፮፥፵፯)።

አንባቢ ሆይ፥ ከላይ በተመለከትነው ታሪክ መሠረት ዛሬም ብዙ ነገሮችን ልንማር እንችላለን። ሐዋርያት በመምህራችው ትዕዛዝ ወደ ቤተ ሳይዳ ሲሄዱ ችግር ቢገጥማቸውም አለፉት ወጀቡንም ተሻገሩት፣ ቢደክሙም አሸነፉት። ሰው በፈጣሪው ትዕዛዝ ሲጓዝ ፈተና አያጋጥመውም አይባልም፣ ያጋጥመዋል። ነገር ግን እንደ ቃሉ ከሄደ ፈተናውን ይሻገረዋል። እንደ ቃሉ ሲሄድ ጌታም እርሱ ባለበት ይሆናል፤ ያዘዋል፤ መከራ የበዛበት ሕይወቱን ስድብ ያስከተለበት አገልግሎቱን ይባርክለታል። በመርከብ፣ በታንኳ የቸገረውን ባሕር እና ሞገድ ጌታ በእግሩ ሲያልፍበት ማየታችን ግሩም ነው። መድኃኒታችን ባሕር ላይ እንደየብስ ተራመደ፤ እኛ በብዙ መሣሪያ ታግዘን ልናሸንፈው የማንችለውን ነገር ጌታችን እንዲሁ ይረታዋል። የሰው ጥበብ፣ ማስተዋል፣ ሀብት ሊያቃልለው ያልቻለውን ጌታ ያለአንዳች መገልገያ መሣሪያ በችሎታው ያቀለዋል። ሐዋርያት በታንኳ መሻገር አቃታቸው ጌታ ግን በእግሩ ተራመደበት፤ ችግሮቻችንን የሚረግጥ በሚያስጨንቀን ላይ የሚሄድ በክፉአችን ላይ የሚራመድ እርሱ ጌታችን ነው።

ሐዋርያት ምትሃት መሰሏቸው፣ እርሱ ግን ጌታ ነበር፤
ሐዋርያት አጥፊ መስሏቸው ደነገጡ፣ እርሱ ግን መድኃኒት ነበር፤
ሐዋርያት በውሃ ላይ ሲራመድ አይተው አያውቁም ነበር፤ ተደነቁ፤

አምላክ በየዕለቱ ለእኛ አዲስ የሆነ ነገር ያደርጋል። ነፍሳችንም በመደነቅ የምታመሰግንበት ነጥብ ከእርሱ ሁልጊዜ ታገኛለህ።

በባሕር ላይ እንደ ደረቅ ለሚራመድ፤ በአስጨናቂዎቻችን ላይ ለሚበረታ፣ በችግራችን ላይ ለሚራመድ፣ እንደ ቃሉ ከሚሄዱ ጋር ለሚጓዝ ጌታ ክብር ምስጋና ይሁን። አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ ...

EthiOrthodox e-mail Outreach **EthiOrthodox@AOL.COM**